# የሻለቃ ሰለሞን አዝብጤ ወልዴ

## አጭር የሕይወት ታሪክ

## Short Biography of

# Major Solomon A. Wolde



1949-2002/ 1957-2010



**የጌታ ፈቃድ ይሁን ብለን ዝም አልን::**

የሐዋርያት ስራ 21፥14

**We ceased, saying, The will of the Lord be done**

Acts 21:14

## የሻለቃ ሰለሞን አዝብጤ አጭር የሕይወት ታሪክ

ሻለቃ ሰለሞን አዝብጤ ከአባቱ ከሙቶ አለአቃ አዝብጤ ወልዴና ከእናቱ ከወ/ሮ ስርጉተ ሁሴን ነሀሴ 11 ቀን 1949 ዓ/ም በሐረር ከተማ ተወለደ። ከዚያም ከቤተሰቡ ጋር ወደ አዲስ አበባ ተዛውሮ ዕድሜው ለትምህርት እንደደረሰ በተስፋ ኮከብ ት/ቤት የአንደኛ ደረጃ ትምህርቱን እስከ በ1964 ዓ/ም ተከታትሏል። ከዚያም የሁለተኛ ደርጃ ትምህርቱን በአዲስ ከተማ አጠቃላይ ከ1965 እስከ 1969 በመማር አጠናቋል።

ሰለሞን የወጣትነት ዕድሜው ለኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ በመማረኩ እንደማንኛውም ወጣት በኢሕአፓ ዙሪያ በመሰባሰብ ያቅሙን ያበረከተና የተሳደደ ግለሰብ ሲሆን ውክቢያው ሲያይልና ሲገፋ በመንገድ ዳር ሬሳው ከሚጣል ሀገሩ ድንበር ላይ መሞትን መርጦ ወደ ውትድርና ዓለም ይገባል።

የ21ኛ ግዜ የሐረር አካዳሚ ዕጩ መኮንኖች ኮርስን በመቀላቀል በወቅቱ የሱማሌ ወራሪ ጦር 700 ኪ.ሜ ድንበር ጥሶ ስለገባ ባጭር ግዜ ውስጥ በም/መ/አለቃነት ኅዳር 01 ቀን 1970 ተመርቆ ወደ ጦር ግንባር ተላከ።

ሰለሞን ለሚወዳት ሀገሩ በተለያዩ የጦር አውደ ግምባሮች ተሰልፎ ያዋጋና የተዋጋ ሲሆን በተለይ በ28 ሜካናይዝድ ብርጌድ ውስጥ በአየር መቃወሚያ ሻለቃ አዛዥነት ፣ ቀጥሎም በብርጌዱ ዘመቻ መኮንነት የሰከነ የውጊያ አመራር በመስጠት ይታወቃል። አያሌ ግዳጆችን በተወርዋሪነት ሲወጣ የነበረው ሰንጥቅ ሜካናይዝድ ብርጌድን በማቋቋምም ከፍተኛ አስተዋጽዖ ካደረጉት ውስጥ አንዱ ሲሆን በኋላም የመንጥር ዕዝ ዘመቻ ረዳት በመሆን በመለብሶ ግምባር ምሽግ ውስጥ ለዓመታት ሲዋጋ ኖሯል።

ሰለሞን በወታደራዊ ካርታ ችሎታው አንቱ የተባለ ፣ክብሩን የጠበቀ ፣ብልህ ፣ ንበዝ አስተባባሪና ተፈቃሪ ከመሆኑም በላይ ጀኔራል መኮንኖች ሳይቀሩ እንደኩያቸው ሲያከብሩት የነበረ ምርጥ የጦር መኮንን ነበር።

ሰለሞን በ1976 ዓ/ም ለከፍተኛ ትምህርት ወደ ሶቭየት ኅብረት ተልኮ አለማቀፋዊ ዕውቅና ባለው የፍሩንዚ የጦር አካዳሚ የአዛዥነትና መምሪያ መኮንንነት ኮርስ /በመውሰድ በማስተርስ ድግሪ በ1980 ዓ/ም ተመርቋል።

ከሞስኮ ተመልሶም ሰራዊቱ እስከፈረሰበት 1983 ዓ/ም በማዕከላዊ ዕዝ ዘመቻ መኮንንነት አገሩን በቅንነት አገልግሏል።

ይህ ከፍተኛ የኤሌክትሮኒክስ ዝንባሌ የነበረው መኮንን ከሰራዊቱ ከተሰናበተ በኋላ ራሱንና ቤተሰቡን ለመርዳት በኔካት የቴክኒክ ማሰልጠኛ ት/ቤት በመግባትም በዲፕሎማ ተመርቋል።

ሰለሞን አዝብጤ እ ኤ አ ጀንዋሪ 29 1991 ዓ/ም ከረጅም ግዜ ጓደኛው ከእናኑ ተሾመ ጋር የጋብቻ ስርዓት በመፈጸም በሚያስቀና ፍቅርና መከባበር አብረው በመኖር በኦገስት 17 / 1994 ዓ/ም ሴት ልጃቸውን ላምሮት ሰለሞንን አፍርተዋል።

ሰለሞን አዝብጤ የነበረበት የስኳር በሽታ ኩላሊቱን ከስራ ውጭ ሊያደርገው ሲቃረብ በወዳጅ ዘመድ ርብርቦሽ ቪዛ አግኝቶ እ ኤ አ ኖቬምበር 3 ቀን 2001 ዓ/ም ወደ አሜሪካ አገር አትላንታ ከተማ ይመጣል። ወዲያው በድንገተኛ ሆስፒታል ገብቶ ነፍስ አድን ዕርዳታ ከተደረገለት በኋላ ከጀንዋሪ 2002 ጀምሮ ሕይወቱ እስካለፈችበት ግዜ ድረስ ለ 8 ዓመታት ዲያሌሲስ በማድረግ ኖሯል።

አንዱ ሕመም ሌላ ችግር እያስከተለ በ 2005 ዓ/ ም የልብ ቀዶ ጥገና የተደረገለት ሲሆን በዚህ ሁሉ ችግር ውስጥ ሲያልፍ በአምላኩ ላይ ያለው ዕምነት ምርኩዝ ሆኖለት፤ የቤተሰቡን ናፍቆት በሆዱ ይዞ ፤በሽታውን እያዳመጠ ፤ ስራ እየሰራ ፤ ማንኛውንም ለኑሮ የሚያስፈልጉትን ነገሮች ሁሉ እየከወነ ሕይወቱን ለብቻው የመራ ታላቅ የጽናት ሰው ነበር።

ሰለሞን የጠየቀው የፖለቲካ ጥገኝነት ከ8 ዓመት በኋላ ተቀባይነት ስላገኘ ቤተሰቡን ለማስመጣት አስፈላጊ ቅጾችን ሞልቶ በማስገባት ለባለቤቱና ለልጁ የኢሚግሬሽንን የቪዛ መቀበያ ጥሪ በመጠባበቅ ላይ እያለ ባልታሰበ ሰዓት ማርች 10/2010 ዓ/ም ንጋት ላይ በአትላንታ አየር ማረፊያ በስራ ላይ እንዳለ በድንገት ሕይወቱ አልፏል።

ይህ ጽኑ የእግዚአብሔር ሰው ሰው በጓደኞቹና በሚያውቁት ሁሉ እጅግ የተወደደ ፣ ለዛ ያለው ተጫዋች ፣ ብዙ ዕውቀትን ያካበተ ፣ ረጋ ያለና ሰላማዊ ሰው ነበር።

ሰለሞን አዝብጤ እጅግ በሚወዳቸው ባለቤቱና ልጁ እንዲሁም የስጋ ዘመዶቹና ጓደኞቹ እየተናፈቀ ሲታሰብ ይኖራል።

አምላክ የሟችን ነፍስ ይማር ።

## Short Biography of Major Solom on Azbite

Major Solomon Azbite, was born from his mother Mrs. Sirgute Hussen and father Lt. Azbite Wolde in Harar, Ethiopia August 1957. At an early age, he moved to the capital Addis Ababa with his parents and attended his elementary and high school at Tesfa kokeb & Addis ketema comprehensive respectively & graduated in 1977.

While attending high school, Solomon was drawn in to the student political movement and made significant contributions to the cause. Because of the circumstances at the time he joined the army choosing to die fighting for his country.

Later, he joined the 21st Harrar academy course, and graduated in a short period of time and became second lieutenant in 1978. Ethiopia was invaded by Somalian forces at the time, and Solomon was sent to the battle front upon graduation.

Solomon served his beloved country as commanding officer for anti-air craft battalion of the 28 Mechanized Brigade, and later as operation officer of the brigade, while demonstrating his excellent leadership in various battle fields with distinction.

Solomon went to the former Soviet Union for higher education in 1984, attended command & staff course in the renowned Frunzi Military Academy and graduated with a master's degree. After returning from Moscow, he served as an operation officer to the central command until he left the Army.

On January 29, 1991 Solomon Azbite married his long time girlfriend Enanu Teshome and together have one daughter, Lamrot Solomon. His love and respect for his wife and daughter was envied by everyone around him.

Because of his love for electronics & to support his family, Solomon went to Necat Technical School and graduated after he left the Army.

Solomon was diabetic and had kidney failure in November 2001, and came to Atlanta to get treatment. After he received immediate treatment, he was told he needed dialysis and was on dialysis for eight years before he died.

With all these medical problems including heart surgery, Solomon was determined to keep working and provide for himself, leading a very independent life without any assistance.

After completing all the necessary immigration procedure, Solomon was waiting with a big hope to unite with his beloved wife and daughter but he died unexpectedly at his place of work at Atlanta International Airport on March 10/2010.

Solomon was courageous, fun to be with, and loved by his wife, daughter, all his family and friends. He will always be in our hearts.



ሰለሞን በልጅነቱ...





ሰለሞን ከባለቤቱ እናኑ ተሾመና ከልጃቸው ላምሮት ሰለሞን ጋር